# መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፣ ምዕራፍ ፡ 1 ።

### ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ የሐካልያ ፡ ልጅ ፡ የነሐምያ ፡ ቃል ፦ በኻያኛው ፡ ዓመት ፡ በካሴሉ ፡ ወር ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤

2 ፤ እኔ ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ሳለኹ ፣ ከወንድሞቼ ፡ አንዱ ፡ ዐናኒ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ከይሁዳ ፡
መጡ ፤ እኔም ፡ የዳኑትን ፡ ከምርኮ ፡ የተረፉትን ፡ የአይሁድን ፡ ነገር ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ነገር ፡ ጠየቅዃቸው ።

3 ፤ እነርሱም ፦ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ያሉት ፡ ከምርኮ ፡ የተረፉት ፡ ቅሬታዎች ፡ በታላቅ ፡ መከራና ፡ ስድብ ፡
አሉ ፤ የኢየሩሳሌምም ፡ ቅጥር ፡ ፈርሷል ፣ በሮቿም ፡ በእሳት ፡ ተቃጥለዋል ፡ አሉኝ ።

4 ፤ ይህንም ፡ ቃል ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ ተቀምጬ ፡ አለቀስኹ ፣ ዐያሌ ፡ ቀንም ፡ አዝን ፡ ነበር ፤ በሰማይም ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡
እጾምና ፡ እጸልይ ፡ ነበር ፣

5 ፤ እንዲህም ፡ አልኹ ፦ አቤቱ ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፣ ለሚወዱኽና ፡ ትእዛዝኽን ፡ ለሚያደርጉ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡
ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፣ ታላቅና ፡ የተፈራኽ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፣

6 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ዛሬ ፡ በፊትኽ ፡ ስለ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ የምጸልየውን ፡ ጸሎት ፡
ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ዦሮኽ ፡ ያድምጥ ፣ ዐይኖችኽም ፡ ይከፈቱ ፤ ባንተ ፡ ላይም ፡ ያደረግነውን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
ኀጢአት ፡ እናዘዝልኻለኹ ፤ እኔና ፡ የአባቴም ፡ ቤት ፡ በድለናል ።

7 ፤ እኛም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ሠርተናል ፤ ለባሪያኽም ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዝኸውን ፡ ትእዛዝና ፡ ሥርዐት ፡ ሕግም ፡
አልጠበቅንም ።

8 ፤ 9 ፤ አኹንም ፡ ብትተላለፉ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እበትናችዃለኹ ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ብትመለሱ ፡ ግን ፡ ትእዛዜንም ፡
ብትጠብቁ ፡ ብታደርጓትም ፣ ከእናንተ ፡ ሰዎች ፡ እስከሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ቢበተኑ ፡ ከዚያ ፡
እሰበስባቸዋለኹ ፣ ስሜም ፡ ይኖርበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መረጥኹት ፡ ስፍራ ፡ አመጣቸዋለኹ ፡ ብለኽ ፡ ለባሪያኽ ፡ ለሙሴ ፡
ያዘዝኸውን ፡ ቃል ፡ እባክኽ ፡ ዐስብ ።

10 ፤ እነዚህም ፡ በታላቅ ፡ ኀይልኽና ፡ በብርቱ ፡ እጅኽ ፡ የተቤዠኻቸው ፡ ባሪያዎችኽና ፡ ሕዝብኽ ፡ ናቸው ።

11 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፣ ዦሮኽ ፡ የባሪያኽን ፡ ጸሎት ፣ ስምኽንም ፡ ይፈሩ ፡ ዘንድ ፡ የሚወዱትን ፣ የባሪያዎችኽን ፡ ጸሎት ፡
ያድምጥ ፤ ዛሬም ፡ ለባሪያኽ ፡ አከናውንለት ፣ በዚህም ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ምሕረትን ፡ ስጠው ። እኔም ፡ ለንጉሡ ፡ ጠጅ ፡
አሳላፊው ፡ ነበርኹ ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፣ ምዕራፍ ፡ 2 ።

### ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ በኻያኛው ፡ ዓመት ፡ በኒሳን ፡ ወር ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በፊቱ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ጠጁን ፡
አንሥቼ ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጠኹት ። ቀድሞ ፡ ግን ፡ በፊቱ ፡ ያለሐዘን ፡ እኖር ፡ ነበር ።

2 ፤ ንጉሡም ፦ ሳትታመም ፡ ፊትኽ ፡ ለምን ፡ ዐዘነ ፧ ይህ ፡ የልብ ፡ ሐዘን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡
አለኝ ። እጅግም ፡ ብዙ ፡ አድርጌ ፡ ፈራኹ ።

3 ፤ ንጉሡንም ፦ ንጉሡ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፤ የአባቶቼ ፡ መቃብር ፡ ያለባት ፡ ከተማ ፡ ተፈታለችና ፣ በሮቿም ፡
በእሳት ፡ ተቃጥለዋልና ፣ ፊቴ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይዘን ፧ አልኹት ።

4 ፤ ንጉሡም ፦ ምን ፡ ትለምነኛለኽ ፧ አለኝ ። እኔም ፡ ወደሰማይ ፡ አምላክ ፡ ጸለይኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ ንጉሡንም ፦ ንጉሡን ፡ ደስ ፡ ቢያሠኘኽ ፥ ባሪያኽም ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ ቢያገኝ ፥ እሠራው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወዳባቶቼ ፡ መቃብር ፡ ከተማ ፡ ስደደኝ ፡ አልኹት ።

6 ፤ ንግሥቲቱም ፡ በአጠገቡ ፡ ተቀምጣ ፡ ሳለች ፡ ንጉሡ ፦ መንገድኽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ፧ መቼስ ፡ ትመለሳለኽ ፧ አለኝ ። ንጉሡም ፡ ይሰደኝ ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ እኔም ፡ ዘመኑን ፡ ቀጠርኹለት ።

7 ፤ ንጉሡንም ፦ ንጉሡ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፥ እስከይሁዳ ፡ አገር ፡ እንዲያደርሱኝ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ላሉት ፡ ገዢዎች ፡ ደብዳቤ ፡ ይሰጠኝ ፤

8 ፤ በቤቱም ፡ አጠገብ ፡ ላለው ፡ ለግንብ ፡ በሮች ፥ ለከተማውም ፡ ቅጥር ፥ ለምገባበትም ፡ ቤት ፡ ዕንጨት ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ለንጉሡ ፡ ዱር ፡ ጠባቂ ፡ ለአሣፍ ፡ ደብዳቤ ፡ ይሰጠኝ ፡ አልኹት ። ንጉሡም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነችው ፡ እንደ ፡ አምላኬ ፡ እጅ ፡ ሰጠኝ ።

9 ፤ በወንዙም ፡ ማዶ ፡ ወዳሉት ፡ አለቃዎች ፡ መጥቼ ፡ የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጠኊቸው ፡ ንጉሡም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃዎችና ፡ ፈረሰኛዎች ፡ ሰደደ ።

10 ፤ ሖሮናዊውም ፡ ሰንባላጥና ፡ ባሪያው ፡ አሞናዊ ፡ ጦብያ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተበሳጩ ።

11 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ደረስኹ ፥ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ተቀመጥኹ ።

12 ፤ በሌሊትም ፡ ተነሣኹ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ኣደርገው ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ ያኖረውን ፡ ለማንም ፡ አላስታወቅኹም ፤ ተቀምጬበት ፡ ከነበረው ፡ እንስሳ ፡ በቀር ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ እንስሳ ፡ አልነበረም ።

13 ፤ በሸለቆውም ፡ በር ፡ ወጣኹ ፥ ወደዘንዶውም ፡ ምንጭና ፡ ወደጕድፍ ፡ መጣያው ፡ በር ፡ ኼድኹ ፤ የፈረሰውንም ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፥ በእሳትም ፡ የተቃጠሉትን ፡ በሮቿን ፡ ተመለከትኹ ።

14 ፤ ወደምንጩም ፡ በርና ፡ ወደንጉሡ ፡ መዋኛ ፡ ዐለፍኹ ፤ ተቀምጬበትም ፡ የነበረው ፡ እንስሳ ፡ የሚያልፍበት ፡ ስፍራ ፡ አልነበረም ።

15 ፤ በሌሊትም ፡ በፈፋው ፡ በኩል ፡ ወጥቼ ፡ ቅጥሩን ፡ ተመለከትኹ ፤ ዘወርም ፡ ብዬ ፡ በሸለቆው ፡ በር ፡ ገባኹ ፥ እንዲሁም ፡ ተመለስኹ ።

16 ፤ ሹማምቱ ፡ ግን ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኼድኹ ፥ ምን ፡ እንዳደረግኹም ፡ አላወቁም ፡ ነበር ፤ ለአይሁድና ፡ ለካህናቱ ፥ ለታላላቆችና ፡ ለሹማምቱም ፥ ሥራም ፡ ይሠሩ ፡ ለነበሩት ፡ ለሌላዎች ፡ ገና ፡ አልተናገርኹም ፡ ነበር ።

17 ፤ እኔም ፦ እኛ ፡ ያለንበትን ፡ ጕስቍልና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ፈረሰች ፥ በሮቿም ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ተቃጠሉ ፡ ታያላችኹ ፤ አኹንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ መሳለቂያ ፡ እንዳንኾን ፡ ኑና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፡ እንሥራ ፡ አልኋቸው ።

18 ፤ የአምላኬም ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ ንጉሡም ፡ የነገረኝን ፡ ቃል ፡ ነገርኋቸው ። እነርሱም ፦ እንነሣና ፡ እንሥራ ፡ አሉ ። እጃቸውንም ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ አበረቱ ።

19 ፤ ሖሮናዊውም ፡ ሰንባላጥ ፥ ባሪያውም ፡ አሞናዊው ፡ ጦብያ ፥ ዐረባዊውም ፡ ጌሳም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ በንቀት ፡ ሣቁብን ፤ ቀላል ፡ አድርገውንም ፦ ይህ ፡ የምታደርጉት ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በእውኑ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ትሸፍቱ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳላችኹን ፧ አሉ ።

20 ፤ እኔም ፡ መልሼ ፦ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ያከናውንልናል ፥ እኛም ፡ ባሪያዎቹ ፡ ተነሥተን ፡ እንሠራለን ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዕድል ፡ ፈንታና ፡ መብት ፡ መታሰቢያም ፡ የላችኹም ፡ አልኋቸው ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ኤልያሴብ ፡ ወንድሞቹም ፡ ካህናት ፡ ተነሥተው ፡ የበግ ፡ በር ፡ ሠሩ ፤ ቀደሱትም ፥ ሳንቃዎቹንም ፡


www.ethiopianorthodox.org

አቆሙ ፤ እስከሃሜአ[239] ፡ ግንብና ፡ እስከሐናንኤል ፡ ግንብ ፡ ድረስ ፡ ቀደሱት ።

2 ፤ በአጠገቡ ፡ የኢያሪኮ ፡ ሰዎች ፡ ሠሩ ፤ በአጠገባቸውም ፡ የአምሪ ፡ ልጅ ፡ ዘኩር ፡ ሠራ ።

3 ፤ የሃስናአ ፡ ልጆችም ፡ የዓሣ ፡ በር ፡ ሠሩ ፤ ሠረገላዎቹን ፡ አኖሩ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፥ ቍልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረጉ ።

4 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የአቆስ ፡ ልጅ ፡ የኦርዮ ፡ ልጅ ፡ ሜሪሞት ፡ ዐደሰ ። በአጠገባቸውም ፡ የሜሴዜቤል ፡ ልጅ ፡ የበራክያ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ ዐደሰ ። በአጠገባቸውም ፡ የበዓና ፡ ልጅ ፡ ሳዶቅ ፡ ዐደሰ ።

5 ፤ በአጠገባቸውም ፡ ቴቁሐውያን ፡ ዐደሱ ፤ ታላላቆቻቸው ፡ ግን ፡ ለጌታቸው ፡ ሥራ ፡ ዐንገታቸውን ፡ አላዋረዱም ።

6 ፤ የፋሴሐ ፡ ልጅ ፡ ዮዳዔና ፡ የበሶድያ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ አሮጌውን ፡ በር ፡ ዐደሱ ፤ ሠረገላዎቹን ፡ አኖሩ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፥ ቍልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረጉ ።

7 ፤ በአጠገባቸውም ፡ ገባዖናዊው ፡ መልጥያና ፡ ሜሮኖታዊው ፡ ያዶን ፥ የወንዙም ፡ ማዶ ፡ አለቃ ፡ ግዛት ፡ የኾኑ ፡ የገባዖንና ፡ የምጽጳ ፡ ሰዎች ፡ ዐደሱ ።

8 ፤ በአጠገባቸውም ፡ ወርቅ ፡ አንጥረኛው ፡ የሐርሃያ ፡ ልጅ ፡ ዑዝኤል ፡ ዐደሰ ። በአጠገቡም ፡ ከሽቱ ፡ ቀማሚዎች ፡ የነበረ ፡ ሐናንያ ፡ ዐደሰ ፤ እስከ ፡ ሰፊው ፡ ቅጥር ፡ ድረስ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ጠገኑ ።

9 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ የሆር ፡ ልጅ ፡ ረፋያ ፡ ዐደሰ ።

10 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የኤርማፍ[240] ፡ ልጅ ፡ ይዳያ ፡ በቤቱ ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ዐደሰ ። በአጠገቡም ፡ የአሰበንያ[241] ፡ ልጅ ፡ ሐጡስ[242] ፡ ዐደሰ ።

11 ፤ የካሪም ፡ ልጅ ፡ መልክያ ፥ የፈሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጅም ፡ ዐሱብ ፡ ሌላውን ፡ ክፍልና ፡ የእቶኑን ፡ ግንብ ፡ ዐደሱ ።

12 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ግዛት ፡ እኩሌታና ፡ የመንደሮቿ ፡ አለቃ ፡ የአሎኤስ[243] ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ዐደሰ ።

13 ፤ ሐኖንና ፡ የዛኖዋ ፡ ሰዎችም ፡ የሸለቆውን ፡ በር ፡ ዐደሱ ፤ ሠሩት ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፥ ቍልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረጉ ፤ ደግሞም ፡ እስከጕድፍ ፡ መጣያው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ የሚኾን ፡ ቅጥር ፡ ሠሩ ።

14 ፤ የቤትሐካሪምም ፡ ግዛት ፡ አለቃ ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ መልክያ ፡ የጕድፍ ፡ መጣያውን ፡ በር ፡ ዐደሰ ፤ ሠራው ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆመ ፥ ቍልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረገ ።

15 ፤ የምጽጳም ፡ ግዛት ፡ አለቃ ፡ የኮልሖዜ ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ የምንጩን ፡ በር ፡ ዐደሰ ፤ ሠራው ፥ ከደነውም ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆመ ፥ ቍልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረገ ፤ ከዳዊትም ፡ ከተማ ፡ እስከሚወርደው ፡ ደረጃ ፡ ድረስ ፡ በንጉሡ ፡ አትክልት ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ የሼላን ፡ መዋኛ ፡ ቅጥር ፡ ሠራ ።

16 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቤትጹር ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ የዓዝቡቅ ፡ ልጅ ፡ ነሐምያ ፡ በዳዊት ፡ መቃብር ፡ አንጻር ፡ እስካለው ፡ ስፍራ ፥ እስከተሠራውም ፡ መዋኛ ፥ እስከኀያላኑም ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ዐደሰ ።

17 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ሌዋውያንና ፡ የባኒ ፡ ልጅ ፡ ሬሁም ፡ ዐደሱ ። በአጠገባቸውም ፡ የቅዒላ ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ ሐሸብያ ፡ ስለ ፡ ግዛቱ ፡ ዐደሰ ።

18 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቅዒላ ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ የኤንሐዳድ ፡ ልጅ ፡ በዋይ ፡ ወንድሞቹም ፡ ዐደሱ ።

19 ፤ በአጠገቡም ፡ የምጽጳ ፡ አለቃ ፡ የኢያሱ ፡ ልጅ ፡ ኤጽር ፡ በማእዘኑ ፡ አጠገብ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቤት ፡ አንጻር ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሰ ።

20 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የዘባይ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ከማእዘኑ ፡ ዠምሮ ፡ እስከታላቁ ፡ ካህን ፡ እስከኤልያሴብ ፡ ቤት ፡

239 ዕብ. ፥ ሜአህ ፡ (ምእት • መቶ) ።
240 ዕብ. ፥ ሐሩማፍ ።
241 ዕብ. ፥ ሐሻብንያሕ ።
242 ዕብ. ፥ ሐጡሽ ።
243 ዕብ. ፥ ሀ ፡ ሎኄሽ ፡ (ለኋሲ • በለኆሳስ ፡ የሚናገረው) ።



www.ethiopianorthodox.org

መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ተግቶ ፡ ዐደሰ ።

21 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የአቆስ ፡ ልጅ ፡ የኦርዮ ፡ ልጅ ፡ ሜሪሞት ፡ ከኤልያሴብ ፡ ቤት ፡ መግቢያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከኤልያሴብ ፡ ቤት ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሰ ።

22 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቈላው ፡ ሰዎች ፡ ካህናቱ ፡ ዐደሱ ።

23 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ብንያምና ፡ ዐሱብ ፡ በቤታቸው ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ዐደሱ ። ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ የመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ዐደሰ ።

24 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የኤንሐደድ[244] ፡ ልጅ ፡ ቢንዊ ፡ ከዐዛርያስ ፡ ቤት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማእዘኑ ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሰ ።

25 ፤ የኡዛይ ፡ ልጅ ፡ ፋላል ፡ በማእዘኑ ፡ አንጻር ፡ ያለውንና ፡ በዘበኞዎች ፡ አደባባይ ፡ አጠገብ ፡ ከላይኛው ፡ የንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ የቆመውን ፡ ግንብ ፡ ሠራ ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የፋሮስ ፡ ልጅ ፡ ፈዳያ ፡ ሠራ ።

26 ፤ ናታኒምም ፡ በዖፌል ፡ በውሃው ፡ በር ፡ አንጻር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወጥቶ ፡ በቆመው ፡ ግንብ ፡ አጠገብ ፡ እስካለው ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጡ ።

27 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ቴቁሐውያን ፡ ወጥቶ ፡ በቆመው ፡ በታላቁ ፡ ግንብ ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ እስከዖፌል ፡ ቅጥር ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሱ ።

28 ፤ ከፈረሱ ፡ በር ፡ በላይ ፡ ካህናቱ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየቤታቸው ፡ አንጻር ፡ ዐደሱ ።

29 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ ሳዶቅ ፡ በቤቱ ፡ አንጻር ፡ ዐደሰ ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የምሥራቁን ፡ በር ፡ ጠባቂ ፡ የሴኬንያ ፡ ልጅ ፡ ሸማያ ፡ ዐደሰ ።

30 ፤ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ ሐናንያና ፡ የሴሌፍ ፡ ስድስተኛው ፡ ልጁ ፡ ሐኖን ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሱ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የበራክያ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ በጓዳው ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ዐደሰ ።

31 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ከወርቅ ፡ አንጥረኛዎቹ ፡ የነበረ ፡ መልክያ ፡ እስከ ፡ ናታኒምና ፡ እስከነጋዴዎቹ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ በሐሚፍቃድ ፡ በር ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ እስከማእዘኑ ፡ መውጫ ፡ ድረስ ፡ ዐደሰ ።

32 ፤ ከማእዘኑም ፡ መውጫ ፡ ዠምረው ፡ እስከበጉ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ወርቅ ፡ አንጥረኛዎችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ዐደሱ ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ ሰንባላጥም ፡ ቅጥሩን ፡ እንደ ፡ ሠራን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ ተበሳጨም ፥ በአይሁድም ፡ አላገጠ ።

2 ፤ በወንድሞቹና ፡ በሰማርያ ፡ ሰራዊትም ፡ ፊት ፦ እነዚህ ፡ ደካማዎች ፡ አይሁድ ፡ የሚሠሩት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይተዉላቸዋልን ፧ ይሠዋሉን ፧ ባንድ ፡ ቀንስ ፡ ይጨርሳሉን ፧ የተቃጠለውንስ ፡ ድንጋይ ፡ ከፍርስራሹ ፡ መልሰው ፡ ያድኑታልን ፧ ብሎ ፡ ተናገረ ።

3 ፤ አሞናዊውም ፡ ጦብያ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሞ ፦ በድንጋይ ፡ በሚሠሩት ፡ ቅጥራቸው ፡ ላይ ፡ ቀበሮ ፡ ቢመጣበት ፡ ያፈርሰዋል ፡ አለ ።

4 ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ተንቀናልና ፥ ስማ ፤ ስድባቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ መልስባቸው ፤ በምርኮ ፡ አገር ፡ ለብዝበዛ ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጣቸው ።

5 ፤ በደላቸውንም ፡ አትክደን ፥ ኀጢአታቸውም ፡ ከፊትኽ ፡ አይደምሰስ ፤ በሠራተኛዎች ፡ ፊት ፡ አስቈጥተውኻልና ።

6 ፤ ቅጥሩንም ፡ ሠራን ፤ ቅጥሩም ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ እኩሌታው ፡ ድረስ ፡ ተጋጠመ ፤ የሕዝቡም ፡ ልብ ፡ ለሥራው ፡ ጨከነ ።

7 ፤ ሰንባላጥና ፡ ጦብያም ፡ ዐረባውያንም ፡ አሞናውያንም ፡ አሽዶዳውያንም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቅጥር ፡ እየታደሰ ፡ እንደ ፡

244ዕብ. ፥ ሔናዳድ ።



www.ethiopianorthodox.org

ኼደ ፥ የፈረሰውም ፡ ሊጠገን ፡ እንደ ፡ ተዠመረ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጡ ።

8 ፤ መጥተውም ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይወጉና ፡ ያሸብሩ ፡ ዘንድ ፡ ዅሉም ፡ በአንድነት ፡ ተማማሉ ።

9 ፤ ወደ ፡ አምላካችንም ፡ ጸለይን ፥ ከነርሱም ፡ የተነሣ ፡ በአንጻራቸው ፡ ተጠባባቂዎች ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ አደረግን ።

10 ፤ ይሁዳም ፦ የተሸካሚዎች ፡ ኀይል ፡ ደከመ ፥ ፍርስራሹም ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ቅጥሩንም ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፡
አሉ ።

11 ፤ ጠላቶቻችንም ፦ ወደ ፡ መካከላቸው ፡ እስክንመጣና ፡ እስክንገድላቸው ፡ ድረስ ፡ ሥራቸውንም ፡ እስክናስተጓጕል ፡
ድረስ ፡ አያውቁምና ፡ አያዩም ፡ አሉ ።

12 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የተቀመጡት ፡ አይሁድ ፡ መጥተው ፦ ከስፍራው ፡ ዅሉ ፡ ይመጡብናል ፡ ብለው ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡
ነገሩን ።

13 ፤ ከቅጥሩም ፡ በስተ፡ዃላ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በታችኛው ፡ ስፍራ ፡ ሰይፋቸውን ፡ ጦራቸውንም ፡ ቀስታቸውንም ፡ አስይዤ ፡
ሕዝቡን ፡ በየወገናቸው ፡ አቆምዃቸው ።

14 ፤ አይቼም ፡ ተነሣኹ ፥ ታላላቆቹንና ፡ ሹማምቱንም ፡ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ፦ አትፍሯቸው ፤ ታላቁንና ፡ የተፈራውን ፡
ጌታ ፡ ዐስቡ ፥ ስለ ፡ ወንድሞቻችኹም ፡ ስለ ፡ ወንዶችና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፡ ስለ ፡ ሚስቶቻችኹም ፡ ስለ ፡
ቤቶቻችኹም ፡ ተዋጉ ፡ አልዃቸው ።

15 ፤ ጠላቶቻችንም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰልን ፥ እግዚአብሔርም ፡ ምክራቸውን ፡ ከንቱ ፡ እንዳደረገው ፡
ሰሙ ፤ እኛም ፡ ዅላችን ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ እያንዳንዳችን ፡ ወደ ፡ ሥራችን ፡ ተመለስን ።

16 ፤ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ብላቴናዎቼ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፥ እኩሌቶቹም ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ቀስትና ፡
ጥሩርም ፡ ይዘው ፡ ነበር ፤ አለቃዎቹም ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ዅሉ ፡ በዃላ ፡ ይቆሙ ፡ ነበር ።

17 ፤ ቅጥሩንም ፡ የሚሠሩትና ፡ ተሸካሚዎቹ ፡ ባንድ ፡ እጃቸው ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፥ ባንድ ፡ እጃቸውም ፡ የጦር ፡
መሣሪያቸውን ፡ ይይዙ ፡ ነበር ።

18 ፤ ዐናጢዎቹም ፡ ዅሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰይፉን ፡ በወገቡ ፡ ታጥቆ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፤ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ የሚነፋ ፡
በአጠገቤ ፡ ነበረ ።

19 ፤ ታላላቆቹንና ፡ ሹማምቱን ፡ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ። ሥራው ፡ ታላቅና ፡ ሰፊ ፡ ነው ፥ እኛም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡
ተበታትነናል ፥ አንዱም ፡ ከኹለተኛው ፡ ርቋል ፤

20 ፤ የቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ድምፅ ፡ ወደምትሰሙበት ፡ ስፍራ ፡ ወደዚያ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ተሰብሰቡ ፤ አምላካችን ፡ ስለ ፡
እኛ ፡ ይዋጋል ፡ አልዃቸው ።

21 ፤ ሥራውንም ፡ ሠራን ፡ ከማለዳ ፡ ወገግታም ፡ ዠምሮ ፡ ከዋክብት ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ጦር ፡ ይይዙ ፡
ነበር ።

22 ፤ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፦ ዅላችኹ ፡ ከብላቴናዎቻችኹ ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡
ዕደሩ ፤ በሌሊትም ፡ ጠባቂዎች ፡ ኹኑልን ፥ በቀንም ፡ ሥሩ ፡ አልዃቸው ።

23 ፤ እኔና ፡ ወንድሞቼም ፡ ብላቴናዎቼም ፡ በዃላዬም ፡ የነበሩት ፡ ጠባቂዎች ፡ ልብሳችንን ፡ አናወልቅም ፡ ነበር ።

________________መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ በወንድሞቻቸውም ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ የሕዝቡና ፡ የሚስቶቻቸው ፡ ጩኸት ፡ ኾነ ።

2 ፤ ዐያሌዎቹም ፦ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችን ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ በልተንም ፡ በሕይወት ፡ እንድንኖር ፡ እኽልን ፡
እንሸምት ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

3 ፤ ዐያሌዎቹም ፦ ከራብ ፡ የተነሣ ፡ እኽልን ፡ እንሸምት ፡ ዘንድ ፡ ዕርሻችንና ፡ ወይናችንን ፡ ቤታችንንም ፡ አስይዘናል ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይሉ ፡ ነበር ።

4 ፤ ሌላዎቹም ፦ ለንጉሡ ፡ ግብር ፡ ዕርሻችንንና ፡ ወይናችንን ፡ አስይዘን ፡ ገንዘብ ፡ ተበድረናል ፤

5 ፤ አኹንም ፡ ሥጋችን ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሥጋ ፥ ልጆቻችንም ፡ እንደ ፡ ልጆቻቸው ፡ ናቸው ፤ እንሆም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችን ፡ ባሪያዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሰጥተናል ፥ ከሴቶችም ፡ ልጆቻችን ፡ ባሪያዎች ፡ ኾነው ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ፤ ታላላቆችም ፡ ዕርሻችንና ፡ ወይናችንን ፡ ይዘዋልና ፥ ልናድናቸው ፡ አንችልም ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

6 ፤ እኔም ፡ ጩኸታቸውንና ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣኹ ።

7 ፤ በልቤም ፡ ዐሰብኹ ፥ ታላላቆቹንና ፡ ሹማምቱንም ፦ ኹላችኹ ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ ወለድ ፡ ትወስዳላችኹ ፡ ብዬ ፡ ተጣላኋቸው ፤ ትልቅም ፡ ጉባኤ ፡ ሰበሰብኹባቸው ።

8 ፤ እኔም ፦ ለአሕዛብ ፡ የተሸጡትን ፡ ወንድሞቻችንን ፡ አይሁድን ፡ በፈቃዳችን ፡ ተቤዠን ፤ እናንተስ ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ ትሸጣላችኹን ፨ እነርሱስ ፡ ለእኛ ፡ የተሸጡ ፡ ይኾናሉን ፨ አልኋቸው ። እነርሱም ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ መልስም ፡ አላገኙም ።

9 ፤ ደግሞም ፡ አልኹ ፦ የምታደርጉት ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ ጠላቶቻችን ፡ አሕዛብ ፡ እንዳይሰድቡን ፡ አምላካችንን ፡ በመፍራት ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ አይገባችኹምን ፨

10 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ ወንድሞቼም ፡ ብላቴናዎቼም ፡ ገንዘብና ፡ እኽል ፡ ለእነርሱ ፡ አበድረናል ፤ እባካችኹ ፥ ይህን ፡ ወለድ ፡ እንተውላቸው ።

11 ፤ ዕርሻቸውንና ፡ ወይናቸውን ፡ ወይራቸውንና ፡ ቤታቸውንም ፡ ከነርሱም ፡ የወሰዳችኹትን ፡ ገንዘቡንና ፡ እኽሉን ፥ ወይን ፡ ጠጁንና ፡ ዘይቱን ፡ ከመቶ ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ እባካችኹ ፡ ዛሬ ፡ መልሱላቸው ።

12 ፤ እነርሱም ፦ እንመልስላቸዋለን ፥ ከነርሱም ፡ ምንም ፡ አንሻም ፤ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ እንዲሁ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉ ። ካህናቱንም ፡ ጠርቼ ፡ እንደዚህ ፡ ነገር ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አማልኋቸው ።

13 ፤ ደግሞም ፡ ልብሴን ፡ አራገፍኹና ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ የማያደርገውን ፡ ሰው ፡ ከቤቱና ፡ ከሥራው ፡ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያራግፈው ፤ እንዲሁም ፡ የተራገፈና ፡ ባዶ ፡ ይኹን ፡ አልኹ ። ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፦ አሜን ፡ አሉ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑ ፤ ሕዝቡም ፡ እንደዚህ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ።

14 ፤ ንጉሡም ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ካዘዘኝ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ከንጉሡ ፡ ከአርጤክስስ ፡ ከኻያኛው ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እኔና ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአለቃ ፡ የሚገባውን ፡ ሥንቅ ፡ አልበላንም ።

15 ፤ ከእኔ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩት ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አክብደው ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ እንጀራውና ፡ ስለ ፡ ወይኑ ፡ አርባ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ ይወስዱ ፡ ነበር ፤ ሎሌዎቻቸውም ፡ ደግሞ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ይሠለጥኑ ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ፈራኹ ፡ እንዲህ ፡ አላደረግኹም ።

16 ፤ ደግሞም ፡ አጥብቄ ፡ የቅጥሩን ፡ ሥራ ፡ ሠራኹ ፥ ዕርሻም ፡ አልገዛንም ፤ ብላቴናዎቼም ፡ ኹሉ ፡ ወደዚያው ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ተሰበሰቡ ።

17 ፤ ደግሞም ፡ በዙሪያችን ፡ ካሉት ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ከመጡት ፡ ሌላ ፡ ከአይሁድና ፡ ከሹማምቱ ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ በገበታዬ ፡ ነበሩ ።

18 ፤ ከወፎችም ፡ በቀር ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ በሬና ፡ ስድስት ፡ የሰቡ ፡ በጎች ፥ በዐሥር ፡ በዐሥር ፡ ቀንም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይዘጋጅልኝ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አገዛዝ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ከብዶ ፡ ነበርና ፥ ለአለቃ ፡ የሚገባውን ፡ ሥንቅ ፡ አልሻም ፡ ነበር ።

19 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ያደረግኹትን ፡ ኹሉ ፡ ለበጎነት ፡ ዐስብልኝ ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምዕራፍ ፡ 6 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ቅጥሩን ፡ እንደ ፡ ሠራኹ ፥ ከፍራሹም ፡ አንዳች ፡ እንዳልቀረበት ፡ ሰንባላጥና ፡ ጦብያ ፡
ዐረባዊውም ፡ ጌሳም ፡ የቀሩትም ፡ ጠላቶቻችን ፡ ሰሙ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በበሮቹ ፡ ውስጥ ፡
ሳንቃዎቹን ፡ አላቆምኹም ፡ ነበር ።

2 ፤ ሰንባላጥና ፡ ጌሳም ፦ መጥተኽ ፡ በኦኖ ፡ ቈላ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መንደሮች ፡ እንገናኝ ፡ ብለው ፡ ላኩብኝ ፤ ነገር ፡
ግን ፥ ክፉ ፡ ያደርጉብኝ ፡ ዘንድ ፡ ያስቡ ፡ ነበር ።

3 ፤ እኔም ፦ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ እሠራለኹ ፥ እወርድም ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፤ ሥራውን ፡ ትቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡
በመውረዴ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሥራው ፡ ይታጐላል ፡፡ ብዬ ፡ መልእክተኛዎችን ፡ ላክኹባቸው ።

4 ፤ እንዲህም ፡ ቃል ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ላኩብኝ ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ቃል ፡ መለስኹላቸው ።

5 ፤ ሰንባላጥም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ ብላቴናውን ፡ ዐምስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ላከብኝ ፤

6 ፤ በእጁም ፡ ውስጥ ፦ አንተና ፡ አይሁድ ፡ ዐመፅ ፡ እንድታስቡ ፥ ስለዚህም ፡ ቅጥሩን ፡ እንድትሠራ ፥ ንጉሣቸውም ፡
ትኾን ፡ ዘንድ ፡ እንድትወድ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ተሰምቷል ።

7 ፤ ደግሞም ፦ ንጉሥ ፡ በይሁዳ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ነቢያትን ፡
አቁመኻል ፤ አኹንም ፡ ለንጉሡ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ያወሩለታል ፤ እንግዲህ ፡ መጥተኽ ፡ በአንድነት ፡ እንማከር ፡ የሚል ፡
ክፍት ፡ ደብዳቤ ፡ ነበረ ።

8 ፤ እኔም ፦ አንተ ፡ ከልብኽ ፡ ፈጥረኽዋል ፡ እንጂ ፡ እንደተናገርኸው ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ የለም ፡ ብዬ ፡ ላክኹበት ።

9 ፤ እነርሱም ፡ ኹሉ ፡ ሥራው ፡ እንዳይፈጸም ፦ እጃቸው ፡ ይደክማል ፡ ብለው ፡ ያስፈራሩን ፡ ዘንድ ፡
ወደዱ ፤ አኹንም ፥ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እጄን ፡ አበርታ ።

10 ፤ እኔም ፡ ወደመሔጣብኤል ፡ ልጅ ፡ ወደድላያ ፡ ልጅ ፡ ወደሽማያ ፡ ቤት ፡ ገባኹ ፤ ርሱም ፡ ተዘግቶ ፡
ነበርና ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ እንገናኝ ፡ የመቅደሱንም ፡ ደጆች ፡ እንዝጋ ፤ እነርሱ ፡ መጥተው ፡
ይገድሉኻልና ፥ በሌሊትም ፡ ይገድሉኽ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣሉና ፡ አለ ።

11 ፤ እኔም ፦ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የሸሽና ፥ ነፍሱንስ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ የገባ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ እኔስ ፡
አልገባም ፡ አልኹት ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ልኮት ፡ እንዳልነበረ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ትንቢት ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ እንሆ ፥ ዐወቅኹ ፤ ጦብያና ፡
ሰንባላጥም ፡ ገዝተውት ፡ ነበር ።

13 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ አደርግና ፡ እበድል ፡ ዘንድ ፥ በእኔም ፡ ላይ ፡ ክፉት ፡ እንዲናገሩና ፡ እንዲያላግጡ ፡ ያስፈራራኝ ፡
ዘንድ ፡ ተገዝቶ ፡ ነበር ።

14 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ሥራቸው ፡ ጦብያንና ፡ ሰንባላጥን ፡ ያስፈራሩኝም ፡ ዘንድ ፡ የወደዱትን ፡ ነቢዪቱን ፡
ኖዓድያን ፡ የቀሩትንም ፡ ነቢያት ፡ ዐስብ ።

15 ፤ ቅጥሩም ፡ በኤሉል ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ተጨረሰ ።

16 ፤ ጠላቶቻችንም ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያችን ፡ የነበሩ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፈሩ ፥ በራሳቸውም ፡ ዐሳብ ፡
እጅግ ፡ ተዋረዱ ፥ ይህም ፡ ሥራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ዐወቁ ።

17 ፤ 18 ፤ ጦብያም ፡ የኤራ ፡ ልጅ ፡ የሴኬንያ ፡ ዐማች ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ ልጁም ፡ ይሆሐናን ፡ የቤራክያን ፡ ልጅ ፡
የሜሱላምን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስላገባ ፥ በይሁዳ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተማምለው ፡ ነበርና ፥ በዚያ ፡ ወራት ፡ ብዙ ፡
የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ ጦብያ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይልኩ ፡ ነበር ፥ የጦብያም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ይመጡ ፡
ነበር ።

19 ፤ ደግሞም ፡ በፊቴ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ መልካም ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፥ ቃሌንም ፡ ያወሩለት ፡ ነበር ፤ ጦብያም ፡ ሊያስፈራራኝ ፡
ደብዳቤዎችን ፡ ይልክ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ቅጥሩ ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ ካቆምኹ ፡ በኋላ ፥ በረኞዎቹና ፡ መዘምራኑ ፡
ሌዋውያኑም ፡ ከተሾሙ ፡ በኋላ ፥

2 ፤ ወንድሜን ፡ ዐናኒንና ፡ የግንቡን ፡ አለቃ ፡ ሐናንያን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ሾምኋቸው ፤ ርሱም ፡ እውነተኛ ፡
ከሌላዎቹም ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

3 ፤ እኔም ፦ ፀሓይ ፡ እስኪሞቅ ፡ ድረስ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ አይከፈቱ ፤ እነርሱም ፡ ቆመው ፡ ሳሉ ፡ ደጆቹን ፡
ይዝጉ ፥ ይቈልፉም ፤ ከኢየሩሳሌምም ፡ ሰዎች ፡ አንዳንዱን ፡ በየተራው ፡ አንዳንዱንም ፡ በየቤቱ ፡ አንጻር ፡ ጠባቂዎችን ፡
አስቀምጡ ፡ አልኋቸው ።

4 ፤ ከተማዪቱም ፡ ሰፊና ፡ ታላቅ ፡ ነበረች ፤ በውስጧ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ፥ ቤቶቹም ፡ አልተሠሩም ፡
ነበር ።

5 ፤ አምላኬም ፡ ታላቆቹንና ፡ ሹማምቱን ፡ ሕዝቡንም ፡ ሰብስቤ ፡ እቈጥራቸው ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ አደረገ ፤ አስቀድመው ፡
የመጡትን ፡ ሰዎች ፡ የትውልድ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ አገኘኹ ፥ በርሱም ፡ እንደዚህ ፡ ተጽፎ ፡ አገኘኹ ።

6 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ከማረካቸው ፡ ምርኮኞዎች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡
እየከተማቸው ፡ የተመለሱት ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

7 ፤ ከዘሩባቤል ፥ ከኢያሱ ፥ ከነሐምያ ፥ ከዐዛርያስ ፥ ከረዓምያ ፥ ከነሐማኒ ፥ ከመርዶክዮስ ፥ ከበላሳን ፥ ከሚስጴሬት ፥ ከበጉ
ዋይ ፥ ከነሑም ፥ ከበዓና ፡ ጋራ ፡ መጡ ።

8 ፤ የእስራኤልም ፡ ሕዝብ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የፋሮስ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ።

9 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ።

10 ፤ የኤራ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

11 ፤ ከኢያሱና ፡ ከኢዮአብ ፡ ልጆች ፡ የኾኑ ፡ የፈሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡
ስምንት ።

12 ፤ የዔላም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

13 ፤ የዛቱዕ ፡ ልጆች ፥ ስምንት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ።

14 ፤ የዘካይ ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ።

15 ፤ የቢንዊ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ስምንት ።

16 ፤ የቤባይ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

17 ፤ የዓዝጋድ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ።

18 ፤ የአዶኒቃም ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ሰባት ።

19 ፤ የበጉዋይ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድሳ ፡ ሰባት ።

20 ፤ የዓዲን ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ዐምስት ።

21 ፤ የሕዝቅያስ ፡ ወገን ፡ የአጤር ፡ ልጆች ፥ ዘጠና ፡ ስምንት ።

22 ፤ የሐሱም ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

23 ፤ የቤሳይ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አራት ።

24 ፤ የሐሪፍ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ።

25 ፤ የገባዖን ፡ ልጆች ፥ ዘጠና ፡ ዐምስት ።



www.ethiopianorthodox.org

26 ፤ የቤተ ፡ ልሔምና ፡ የነጦፋ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ስምንት ።

27 ፤ የዓናቶች ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

28 ፤ የቤትዓዝሞት ፡ ሰዎች ፥ አርባ ፡ ኹለት ።

29 ፤ የቂርያትይዓሪምና ፡ የከፊራ ፡ የብኤሮትም ፡ ሰዎች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሦስት ።

30 ፤ የራማና ፡ የጌባ ፡ ሰዎች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አንድ ።

31 ፤ የማክማስ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ።

32 ፤ የቤቴልና ፡ የጋይ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

33 ፤ የኹለተኛው ፡ ናባው ፡ ሰዎች ፥ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

34 ፤ የኹለተኛው ፡ ዔላም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

35 ፤ የካሪም ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ።

36 ፤ የኢያሪኮ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡

37 ፤ የሎድና ፡ የሐዲድ ፡ የኦኖም ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አንድ ።

38 ፤ የሴናዓ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ።

39 ፤ ካህናቱ ፤ ከኢያሱ ፡ ወገን ፡ የዮዳዔ ፡ ልጆች ፥ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ።

40 ፤ የኢሜር ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

41 ፤ የፋስኮር ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ።

42 ፤ የካሪም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ።

43 ፤ ሌዋውያኑ ፤ ከሆዳይዋ ፡ ወገን ፡ የኢያሱና ፡ የቀድምኤል ፡ ልጆች ፥ ሰባ ፡ አራት ።

44 ፤ መዘምራኑ ፤ የአሣፍ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ አርባ ፡ ስምንት ።

45 ፤ በረኞቹ ፤ የሰሎም ፡ ልጆች ፥ የአጤር ፡ ልጆች ፥ የጤልሞን ፡ ልጆች ፥ የዐቁብ ፡ ልጆች ፥ የሐጢጣ ፡
ልጆች ፥ የሰባይ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ።

46 ፤ ናታኒም ፥ የሲሐ ፡ ልጆች ፥ የሐሡፋ ፡ ልጆች ፥

47 ፤ የጠብዖት ፡ ልጆች ፥ የኬራስ ፡ ልጆች ፥ የሲዓ ፡ ልጆች ፥

48 ፤ የፋዶን ፡ ልጆች ፥ የልባና ፡ ልጆች ፥

49 ፤ የአጋባ ፡ ልጆች ፥ የሰምላይ ፡ ልጆች ፥ የሐናን ፡ ልጆች ፥ የጌዴል ፡ ልጆች ፥ የጋሐር ፡ ልጆች ፥

50 ፤ የራያ ፡ ልጆች ፥ የረአሶን ፡ ልጆች ፥ የኔቆዳ ፡ ልጆች ፥

51 ፤ የጋሴም ፡ ልጆች ፥ የዖዛ ፡ ልጆች ፥ የፋሴሐ ፡ ልጆች ፥

52 ፤ የቤሳይ ፡ ልጆች ፥ የምዑናውያን ፡ ልጆች ፥

53 ፤ የንፉሰሲም ፡ ልጆች ፥ የበቅቡቅ ፡ ልጆች ፥ የሐቀፋ ፡ ልጆች ፥ የሐርሑር ፡ ልጆች ፥

54 ፤ የበስሎት ፡ ልጆች ፥ የምሒዳ ፡ ልጆች ፥ የሐርሻ ፡ ልጆች ፥

55 ፤ የበርቆስ ፡ ልጆች ፥ የሢሣራ ፡ ልጆች ፥

56 ፤ የቴማ ፡ ልጆች ፥ የንስያ ፡ ልጆች ፥ የሐጢፋ ፡ ልጆች ።

57 ፤ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፤ የሶጣይ ፡ ልጆች ፥ የሶፌሬት ፡ ልጆች ፥ የፍሩዳ ፡ ልጆች ፥



www.ethiopianorthodox.org

58 ፤ የየዕላ ፡ ልጆች ፥ የደርቆን ፡ ልጆች ፥ የጌዴል ፡ ልጆች ፥

59 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፥ የሐጢል ፡ ልጆች ፥ የፈከራት ፡ ልጆች ፥ የሐፂቦይም ፡ ልጆች ፥ የዐሞን ፡ ልጆች ።

60 ፤ ናታኒም ፡ ኹሉና ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

61 ፤ ከቴልሜላ ፥ ከቴላሬሳ ፥ ከክሩብ ፥ ከአዳን ፥ ከኢሜር ፡ የወጡ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቶቻቸውን ፡ ቤቶችና ፡ ዘራቸውን ፡ ወይም ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ መኾናቸውን ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፤

62 ፤ የዳላያ ፡ ልጆች ፥ የጦብያ ፡ ልጆች ፥ የኔቆዳ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ኹለት ።

63 ፤ ከካህናቱም ፡ የኤብያ ፡ ልጆች ፥ የአቆስ ፡ ልጆች ፥ ከገለዓዳዊው ፡ ከቤርዜሊ ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፡ በስሙም ፡ የተጠራ ፡ የቤርዜሊ ፡ ልጆች ።

64 ፤ እነዚህ ፡ በትውልድ ፡ መጽሐፍ ፡ ትውልዳቸውን ፡ ፈለጉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልተገኘም ፤ ከክህነትም ፡ ተከለከሉ ።

65 ፤ ሐቴርሰታም ፦ በኡሪምና ፡ በቱሚም ፡ የሚፈርድ ፡ ካህን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፥ ከተቀደሰው ፡ ነገር ፡ አትበሉም ፡ አላቸው ።

66 ፤ 67 ፤ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ከነበሩ ፡ ከሎሌዎቻቸውና ፡ ከገረዶቻቸው ፡ ሌላ ፡ ጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነበሩ ፤ ኹለቱ ፡ መቶም ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ መዘምራን ፡ ነበሯቸው ።

68 ፤ ፈረሶቻቸውም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፥ በቅሎዎቻቸውም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፥

69 ፤ ግመሎቻቸውም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፥ አህያዎቻቸውም ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ነበሩ ።

70 ፤ ከአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎችም ፡ ዐያሌዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ስጦታ ፡ ሰጡ ። ሐቴርሰታም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክ ፥ ዐምሳም ፡ ድስቶች ፥ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳም ፡ የካህናት ፡ ልብስ ፡ በቤተ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ሰጠ ።

71 ፤ ከአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎችም ፡ ዐያሌዎቹ ፡ በሥራው ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክ ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶም ፡ ምናን ፡ ብር ፡ ሰጡ ።

72 ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ የሰጡት ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክና ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ምናን ፡ ብር ፥ ስድሳ ፡ ሰባትም ፡ የካህናት ፡ ልብስ ፡ ነበረ ።

73 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፥ በረኛዎቹና ፡ መዘምራኑም ፡ ከሕዝቡም ፡ ዐያሌዎቹ ፥ ናታኒምም ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ተቀመጡ ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ ሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ነበሩ ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በውሃው ፡ በር ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ አደባባይ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኾነው ፡ ተሰበሰቡ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ያዘዘውን ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ጸሓፊውን ፡ ዕዝራን ፡ ተናገሩት ።

2 ፤ ካህኑም ፡ ዕዝራ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ሕጉን ፡ በማኅበሩ ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ አስተውለውም ፡ በሚሰሙት ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ አመጣው ።

3 ፤ በውሃውም ፡ በር ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የሚያስተውሉም ፡ ሲሰሙ ፥ ከማለዳ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ድረስ ፡ አነበበው ፤ የሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ዦሮ ፡ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመስማት ፡ ያደምጥ ፡ ነበር ።

4 ፤ ጸሓፊውም ፡ ዕዝራ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በተሠራ ፡ በዕንጨት ፡ መረባርብ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በአጠገቡ ፡
መቲትያ ፥ ሽማዕ ፥ ዐናያ ፥ ኦርዮ ፥ ኬልቅያስ ፥ መዕሴያ ፡ በቀኙ ፡
በኩል ፥ ፈዳያ ፥ ሚሳኤል ፥ መልክያ ፥ ሐሱም ፥ ሐሽበዳና ፥ ዘካርያስ ፥ ሜሱላም ፡ በግራው ፡ በኩል ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

5 ፤ ዕዝራም ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ መጽሐፉን ፡ ገለጠ ፤ በገለጠውም ፡ ጊዜ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ቆሙ ።

6 ፤ ዕዝራም ፡ ታላቁን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባረከ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እጃቸውን ፡ እየዘረጉ ፦ አሜን ፣ አሜን ፡
ብለው ፡ መለሱ ። ራሳቸውንም ፡ አዘነበሉ ፣ በግንባራቸውም ፡ ተደፍተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰገዱ ።

7 ፤ ደግሞ ፡ ኢያሱና ፡
ባኒ ፣ ሰራብያ ፣ ያሚን ፣ ዐቁብ ፣ ሳባታይ ፣ ሆዲያ ፣ መዕሴያ ፣ ቆሊጣስ ፣ ዐዛርያስ ፣ ዮዛባት ፣ ሐናን ፣ ፌልያ ፣ ሌዋውያኑ
ም ፡ ሕጉን ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ በየስፍራቸው ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

8 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ አነበቡ ፤ ዕዝራም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡ ያስተምርና ፡ ያስታውቅ ፡
ነበር ፣ ሕዝቡም ፡ የሚነበበውን ፡ ያስተውሉ ፡ ነበር ።

9 ፤ ሐቴርሰታ ፡ ነሐምያም ፡ ጸሓፊውም ፡ ካህኑ ፡ ዕዝራ ፡ ሕዝቡንም ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፦ ዛሬ ፡
ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ አታልቅሱ ፡ እንባም ፡ አታፍስሱ ፡ አሏቸው ፤ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡
የሕጉን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበርና ።

10 ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፣ የሰባውንም ፡ ብሉ ፣ ጣፋጩንም ፡ ጠጡ ፣ ለእነዚያም ፡ ላልተዘጋጀላቸው ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸውን ፡
ስደዱ ፤ ዛሬ ፡ ለጌታችን ፡ የተቀደሰ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ደስታ ፡ ኀይላችኹ ፡ ነውና ፣ አትዘኑ ፡ አላቸው ።

11 ፤ ሌዋውያንም ፦ ቀኑ ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፣ ዝም ፡ በሉ ፣ አትዘኑም ፡ ብለው ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ጸጥ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

12 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ የተነገረላቸውን ፡ ቃል ፡ አስተውለዋልና ፣ ሊበሉና ፡ ሊጠጡ ፣ ዕድል ፡ ፈንታም ፡ ሊሰዱ ፡
ደስታም ፡ ሊያደርጉ ፡ ኼዱ ።

13 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ካህናቱም ፡ ሌዋውያኑም ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡
ይተረጉምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጸሓፊው ፡ ወደ ፡ ዕዝራ ፡ ተሰበሰቡ ።

14 ፤ 15 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ባለው ፡ በዓል ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በዳስ ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ በከተማዎቻቸውና ፡
በኢየሩሳሌምም ፦ ወደ ፡ ተራራ ፡ ኺዱ ፤ የዘይትና ፡ የበረሓ ፡ ወይራ ፡ የባርሰነትም ፡ የዘንባባም ፡ የለመለመውን ፡ ዛፍ ፡
ቅርንጫፍ ፡ አምጡ ፣ እንደ ፡ ተጻፈውም ፡ ዳሶችን ፡ ሥሩ ፡ ብለው ፡ ይናገሩ ፡ ያውጁም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡
እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎ ፡ አገኙ ።

16 ፤ ሕዝቡም ፡ ወጥተው ፡ አመጡ ፤ እያንዳንዱም ፡ በቤቱ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፣ በአደባባዩም ፡ ላይ ፣ በእግዚአብሔርም ፡
ቤት ፡ አደባባዩ ፡ ላይ ፣ በውሃውም ፡ በር ፡ አደባባይና ፡ በኤፍሬም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ዳስ ፡ ሠራ ።

17 ፤ ከምርኮም ፡ የተመለሱት ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ዳስ ፡ ሠሩ ፣ በዳሱም ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ። ከነዌም ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡
ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አላደረጉም ፡ ነበር ። እጅግም ፡ ታላቅ ፡
ደስታ ፡ ኾነ ።

18 ፤ ከመዠመሪያውም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡
መጽሐፍ ፡ ያነብ ፡ ነበር ። በዓሉን ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ አደረጉ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ የተቀደሰ ፡
ጉባኤ ፡ ነበረ ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፣ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ በዚህም ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጾመው ፣ ማቅም ፡ ለብሰው ፣ በላያቸውም ፡ ትቢያ ፡
ነስንሰው ፡ ተከማቹ ።

2 ፤ የእስራኤልም ፡ ዘር ፡ ከእንግዳዎች ፡ ኹሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ለዩ ፣ ቆመውም ፡ ኀጢአታቸውንና ፡ የአባቶቻቸውን ፡
ኀጢአት ፡ ተናዘዙ ።

3 ፤ በየስፍራቸውም ፡ ቆመው ፡ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ የቀን ፡ ሩብ ፡ ያኽል ፡
አነበቡ ፤ ሦስት ፡ የቀን ፡ ሩብም ፡ ያኽል ፡ ተናዘዙ ፣ ለአምላካቸው ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ሰገዱ ።



www.ethiopianorthodox.org

4 ፤ ሌዋውያኑም ፡ ኢያሱና ፡ ባኒ ፥ ቀድምኤል ፥ ሰበንያ ፥ ቡኒ ፥ ሰራብያ ፥ ባኒ ፥ ክናኒ ፡ በደረጃዎች ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡
ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኹ ።

5 ፤ ሌዋውያኑም ፡ ኢያሱ ፥ ቀድምኤል ፥ ባኒ ፥ አሰበንያ ፥ ሰራብያ ፥ ሆዲያ ፥ ሰበንያ ፥ ፈታያ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ቆማችኍ ፡
ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ። እንዲህም ፡ በሉ ። በበረከትና ፡ በምስጋና ፡ ኹሉ ፡
ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ ክቡር ፡ ስምኽ ፡ ይባረክ ።

6 ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኽ ፤ ሰማዩንና ፡ የሰማያት ፡ ሰማይን ፡ ሰራዊታቸውንም ፡ ኹሉ ፥ ምድሩንና ፡ በርሷ ፡
ላይ ፡ ያሉትን ፡ ኹሉ ፥ ባሕሮቹንና ፡ በእነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፥ ፈጥረኻል ፥ ኹሉንም ፡ ሕያው ፡
አድርገኸዋል ፤ የሰማዩም ፡ ሰራዊት ፡ ለአንተ ፡ ይሰግዳሉ ።

7 ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ አብራምን ፡ መረጥኽ ፥ ከኡር ፡ ከላውዴዎንም ፡ አወጣኸው ፥ ስሙንም ፡
አብርሃም ፡ አልኸው ፤

8 ፤ ልቡም ፡ በፊትኽ ፡ የታመነ ፡ ኾኖ ፡ አገኘኸው ፤ የከነዓናዊውንና ፡ የኬጢያዊውን ፡ የአሞራዊውንም ፡ የፌርዛዊውንም ፡
የኢያቡሳዊውንም ፡ የጌርጌሳዊውንም ፡ ምድር ፡ ለርሱና ፡ ለዘሩ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረግኽ ፡
አንተም ፡ ጻድቅ ፡ ነኽና ፥ ቃልኽን ፡ ፈጸምኽ ።

9 ፤ በግብጽም ፡ ሳሉ ፡ የአባታችንን ፡ መከራ ፡ አየኽ ፥ በቀይ ፡ ባሕርም ፡ ሳሉ ፡ ጩኸታቸውን ፡ ሰማኽ ፤

10 ፤ እንደ ፡ ታበዩባቸውም ፡ ዐውቀኽ ፡ ነበርና ፥ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ኹሉ ፡ በምድሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡
ምልክትና ፡ ተኣምራት ፡ አሳየኽ ፤ ዛሬም ፡ እንደ ኾነው ፡ ስምኽን ፡ አስጠራኽ ።

11 ፤ ከፊታቸውም ፡ ባሕሩን ፡ ከፈልኽ ፥ በባሕሩም ፡ መካከል ፡ በደረቅ ፡ አልፉ ፤ ጠላቶቻቸውን ፡ ግን ፡ ድንጋይ ፡
ለጥልቅ ፡ ውሃ ፡ እንዲጣል ፡ በቀላይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልኻቸው ።

12 ፤ የሚኼዱበትንም ፡ መንገድ ፡ ታበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ በቀን ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፥ በሌሊትም ፡ በእሳት ፡ ዐምድ ፡
መራኻቸው ።

13 ፤ ወደሲናም ፡ ተራራ ፡ ወረድኽ ፥ ከሰማይም ፡ ተናገርኻቸው ፤ ቅኑን ፡ ፍርድና ፡ እውነቱን ፡ ሕግ ፡ መልካሙንም ፡
ሥርዐትና ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠኻቸው ፤

14 ፤ የተቀደሰውንም ፡ ሰንበትኽን ፡ አስታወቅኻቸው ፥ ትእዛዝንና ፡ ሥርዐትን ፡ ሕግንም ፡ በባሪያኽ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡
አዘዝኻቸው ።

15 ፤ ለራባቸውም ፡ ከሰማይ ፡ እንጀራ ፡ ሰጠኻቸው ፥ ለጥማታቸውም ፡ ከአለቱ ፡ ውሃ ፡
አመጣኽላቸው ፤ ወደማልኽላቸውም ፡ ምድር ፡ ገብተው ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኻቸው ።

16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱና ፡ አባቶቻችን ፡ ታበዩ ፥ ዐንገታቸውንም ፡ አደነደኑ ፥ ትእዛዝኽንም ፡ አልሰሙም ፥

17 ፤ ለመስማትም ፡ እንቢ ፡ አሉ ፥ ያደረግኽላቸውንም ፡ ተኣምራት ፡ አላሰቡም ፤ ዐንገታቸውንም ፡
አደነደኑ ፥ በዐመፃቸውም ፡ ወደ ፡ ባርነታቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አለቃ ፡ አደረጉ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፥ ቸርና ፡
መሓሪ ፡ አምላክ ፥ ለቍጣም ፡ የምትዘገይ ፥ ምሕረትንም ፡ የምታበዛ ፡ ነኽ ፥ አልተውኻቸውም ።

18 ፤ ቀልጦ ፡ የተሠራውንም ፡ እንቦሳ ፡ አድርገው ፡— ከግብጽ ፡ ያወጣኽ ፡ አምላክኽ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፥ እጅግም ፡
ባስቈጡኽ ፡ ጊዜ ፥

19 ፤ አንተ ፡ በምሕረትኽ ፡ ብዛት ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ አልተውኻቸውም ፤ በመንገድም ፡ ይመራቸው ፡ ዘንድ ፡ የደመና ፡
ዐምድ ፡ በቀን ፥ የሚኼዱበትንም ፡ መንገድ ፡ ያበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ የእሳት ፡ ዐምድ ፡ በሌሊት ፡ ከነርሱ ፡ አልራቀም ።

20 ፤ ያስተምራቸውም ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ መንፈስኽን ፡ ሰጠኻቸው ፥ መናኽንም ፡ ከአፋቸው ፡
አልከለከልኽም ፥ ለጥማታቸውም ፡ ውሃ ፡ ሰጠኻቸው ።

21 ፤ አርባ ፡ ዓመትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መገብኻቸው ፥ ምንም ፡ አላጡም ፤ ልብሳቸውም ፡ አላረጀም ፥ እግራቸውም ፡
አላበጠም ።



www.ethiopianorthodox.org

22 ፤ መንግሥታትንና ፡ አሕዛብን ፡ ከፍለኽ ፡ ሰጠኻቸው ፤ የሐሴቦንን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎንን ፡ ምድር ፥ የባሳንንም ፡ ንጉሥ ፡
የዐግን ፡ ምድር ፡ ወረሱ ።

23 ፤ ልጆቻቸውንም ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ አበዛኽ ፤ ይገቡና ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡
ወደተናገርኽላቸውም ፡ ምድር ፡ አገባኻቸው ።

24 ፤ ልጆቹም ፡ ገብተው ፡ ምድሩን ፡ ወረሱ ፥ የምድሩን ፡ ሰዎች ፡ ከነዓናውያንን ፡ በፊታቸው ፡
አዋረድኽ ፤ የሚወዱትንም ፡ ነገር ፡ ያደረጉባቸው ፡ ዘንድ ፡ እነርሱንና ፡ ነገሥታታቸውን ፡ የምድሩንም ፡ አሕዛብ ፡
በእጃቸው ፡ አሳልፈኽ ፡ ሰጠኻቸው ።

25 ፤ ምሽጎቹንም ፡ ከተማዎች ፡ የሰባውንም ፡ ምድር ፡ ወሰዱ ፤ መልካሙን ፡ ነገር ፡ የሞሉትን ፡ ቤቶች ፥ የተማሱትንም ፡
ጕድጓዶች ፥ ወይናቹንና ፡ ወይራዎቹን ፡ ብዙዎቹንም ፡ የፍሬ ፡ ዛፎች ፡ ወረሱ ፤ በሉም ፥ ጠገቡም ፥ ወፈሩም ፥ በታላቅ ፡
በጎነትኽም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንቢተኛዎች ፡ ነበሩ ፥ ዐመፁብኽም ፥ ሕግኽንም ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ጣሉት ፤ ወዳንተም ፡ ይመለሱ ፡
ዘንድ ፡ የመሰከሩባቸውን ፡ ነቢያትኽን ፡ ገደሉ ፥ እጅግም ፡ አስቈጡኽ ።

27 ፤ ስለዚህ ፥ ለጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ሰጠኻቸው ፥ አስጨነቋቸውም ፤ በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡
ጮኹ ፥ ከሰማይም ፡ ሰማኻቸው ፤ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ ብዛት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ያዳኗቸውን ፡ ታዳጊዎችን ፡
ሰጠኻቸው ።

28 ፤ ባረፉም ፡ ጊዜ ፡ ተመልሰው ፡ በፊትኽ ፡ ክፉ ፡ አደረጉ ፤ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡
ተውኻቸው ፥ ገዟቸውም ፤ ተመልሰውም ፡ ወዳንተ ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ ከሰማይ ፡ ሰማኻቸው ፥ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡
ብዛት ፡ ታደግኻቸው ፤

29 ፤ ወደ ፡ ሕግኽም ፡ ትመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡ አስመሰከርኽባቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ታበዩ ፥ ትእዛዝኽንም ፡
አልሰሙም ፥ ሰውም ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ የሚኖርበትን ፡ ፍርድኽን ፡ ተላለፉ ፤ ትከሻቸውንም ፡
ሰጡ ፥ ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ፥ አልሰሙምም ።

30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ታገሥኻቸው ፥ በነቢያትኽም ፡ እጅ ፡ በመንፈስኽ ፡
መሰከርኽባቸው ፤ አላደመጡም ፥ ስለዚህም ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ሰጠኻቸው ።

31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ቸርና ፡ መሐሪ ፡ አምላክ ፡ ነኽና ፥ በምሕረትኽ ፡ ብዛት ፡ ፈጽመኽ ፡
አላጠፋኻቸውም ፥ አልተውኻቸውምም ።

32 ፤ አኹንም ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፡ ታላቅና ፡ ኀያል ፡ የተፈራኸውም ፡
አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከአሶር ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእኛና ፡ በነገሥታታችን ፡ በአለቃዎቻችንም ፡
በካህናታችንም ፡ በነቢያታችንም ፡ በአባቶቻችንም ፡ በሕዝብኽ ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ መከራ ፡ ዅሉ ፡ በፊትኽ ፡ ጥቂት ፡
መስሎ ፡ አይታይኽ ።

33 ፤ በደረሰብንም ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፥ አንተ ፡ እውነት ፡ አድርገኻልና ፥ እኛም ፡ ኀጢአት ፡
አድርገናል ።

34 ፤ ነገሥታታችንም ፡ አለቃዎቻችንም ፡ ካህናታችንም ፡ አባቶቻችንም ፡ ሕግኽን ፡ አልጠበቁም ፥ የመሰከርኽባቸውንም ፡
ትእዛዝኽንና ፡ ምስክርኽን ፡ አልሰሙኽም ።

35 ፤ በመንግሥታቸውም ፡ በሰጠኻቸውም ፡ ታላቅ ፡ በጎነትኽ ፥ በፊታቸውም ፡ በሰጠኸው ፡ በሰባው ፡ ምድር ፡
አላመለኩኽም ፥ ከክፉም ፡ ሥራቸው ፡ አልተመለሱም ።

36 ፤ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፤ ፍሬዋንና ፡ በረከቷን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠኻት ፡
ምድር ፥ እንሆ ፥ በርሷ ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፥

37 ፤ ስለ ፡ ኀጢአታችንም ፡ ለሾምኽብን ፡ ነገሥታት ፡ በረከቷን ፡ ታበዛለች ፤ ሰውነታችንንም ፡
ይገዛሉ ፥ በእንስሳዎቻችንም ፡ የሚወዱትን ፡ ያደርጋሉ ፥ እኛም ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡ ላይ ፡ ነን ።



www.ethiopianorthodox.org

38 ፤ ስለዚህም ፡ ኹሉ ፡ የታመነውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገን ፡ እንጽፋለን ፤ አለቃዎቻችንም ፡ ሌዋውያናችንም ፡ ካህናታችንም ፡ ያትሙበታል ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ ያተሙትም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የሐካልያ ፡ ልጅ ፡ ሐቴርሰታ ፡ ነሐምያ ፥

2 ፤ ሴዴቅያስ ፥ ሰራያ ፥

3 ፤ ዐዛርያስ ፥ ኤርምያስ ፥ ፋስኮር ፥ አማርያ ፥ መልክያ ፥

4 ፤ 5 ፤ ሐጡስ ፥ ሰበንያ ፥ መሉክ ፥ ካሪም ፥

6 ፤ ሜሪሞት ፥ ዐብድዩ ፥ ዳንኤል ፥ ጌንቶን ፥ ባሮክ ፥

7 ፤ 8 ፤ ሜሱላም ፥ አብያ ፥ ሚያሚን ፥ መዓዝያ ፥ ቤልጋል ፥ ሸማያ ፤ እነዚህ ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ።

9 ፤ ሌዋውያኑም ፤ የአዛንያ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ ከኤንሐዳድ ፡ ልጆች ፡ ቢንዊ ፥ ቀድምኤል ፤

10 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ሰባንያ ፥ ሆዲያ ፥ ቆሊጣስ ፥

11 ፤ ፊልያ ፥ ሐናን ፥ ሚካ ፥ ረአብ ፥ ሐሸብያ ፥

12 ፤ 13 ፤ ዘኩር ፥ ሰራብያ ፥ ሰበንያ ፥ ሆዲያ ፥ ባኒ ፥ ብኒኑ ።

14 ፤ የሕዝቡ ፡ አለቃዎች ፤ ፋሮስ ፥ ፊሐት ፡ ሞዐብ ፥

15 ፤ ዔላም ፥ ዛቱዕ ፥ ባኒ ፥ ቡኒ ፥ ዓዝጋድ ፥ ቤባይ ፥

16 ፤ 17 ፤ አዶንያስ ፥ በጉዋይ ፥ ዓዲን ፥ አጤር ፥ ሕዝቅያስ ፥

18 ፤ ዓዙር ፥ ሆዲያ ፥ ሐሱም ፥ ቤሳይ ፥

19 ፤ ሐሪፍ ፥ ዐናቶት ፥ ኖባይ ፥

20 ፤ መግጺዓስ ፥ ሜሱላም ፥ ኤዚር ፥

21 ፤ ሜሴዜቤል ፥ ሳዶቅ ፥ ያዱአ ፥

22 ፤ ፈላጥያ ፥ ሐናን ፥ ዐናያ ፥

23 ፤ ሆሴዕ ፥ ሐናንያ ፥ ዐሱብ ፥

24 ፤ 25 ፤ አሎኤስ ፥ ፈልሃ ፥ ሶቤቅ ፥ ሬሁም ፥ ሐሰብና ፥

26 ፤ 27 ፤ መዕሴያ ፥ አኪያ ፥ ሐናን ፥ ዐናን ፥ መሉክ ፥ ካሪም ፥ በዓና ።

28 ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፥ ካህናቱም ፥ ሌዋውያኑም ፥ በረኛዎቹም ፥ መዘምራንም ፥ ናታኒምም ፥ ከምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ራሳቸውን ፡ የለዩ ፡ ኹሉ ፥ ሚስቶቻቸውም ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፥ የሚያውቁትና ፡ የሚያስተውሉትም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ወደ ፡ ታላላቆቻቸው ፡ ተጠጉ ፤

29 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ በተሰጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፥ የጌታችንንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ፍርዱንም ፡ ሥርዐቱንም ፡ ይጠብቁና ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ርግማንና ፡ መሐላውን ፡ አደረጉ ።

30 ፤ ሴቶች ፡ ልጆቻችንንም ፡ ለምድር ፡ አሕዛብ ፡ አንሰጥም ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ለልጆቻችን ፡ አንወስድም ፤

31 ፤ የምድርን ፡ አሕዛብ ፡ ሸቀጥና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እኽል ፡ ሊገበዩ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ቢያመጡ ፥ በሰንበት ፡ ወይም ፡ በተቀደሰው ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ አንገዛም ፤ የሰባተኛውንም ፡ ዓመት ፡ ፍሬና ፡ ዕዳን ፡ ማስከፈል ፡ እንተዋለን ፡ ብለው ፡ ማሉ ።

32 ፤ 33 ፤ ስለአምላካችንም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፥ ስለ ፡ ገጸ ፡ ኅብስትም ፥ ዘወትርም ፡ በሰንበትና ፡ በመባቻ ፡ ስለ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ማቅረብ ፡ ስለእኽሉ ፡ ቍርባንና ፡ ስለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፥ ስለ ፡ በዓላትም ፥ ስለ ፡ ተቀደሱትም ፡ ነገሮች ፥ ለእስራኤልም ፡ ስለሚያስተሰርየው ፡ ስለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ስለአምላካችንም ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በየዓመቱ ፡ የሰቅል ፡ ሢሶ ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዝ ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ አደረግን ።

34 ፤ እኛም ፥ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ ሕዝቡም ፥ እንደ ፡ አባቶቻችን ፡ ቤቶች ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በየዓመቱ ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ አምጥተን ፡ በሕጉ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ይቃጠል ፡ ዘንድ ፡ ስለዕንጨት ፡ ቍርባን ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣልን ፤

35 ፤ በየዓመቱም ፡ የመሬታችንን ፡ በኵራት ፡ የኹሉ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፡ የፍሬ ፡ ኹሉ ፡ በኵራት ፡ ኹሉ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፥

36 ፤ በሕጉም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የልጆቻችንና ፡ የእንስሳዎቻችንን ፡ በኵራት ፥ የበሬዎቻችንንና ፡ የበጎቻችንን ፡ በኵራት ፡ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ ወደሚያገለግሉት ፡ ካህናት ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፥

37 ፤ የእኽላችንንም ፡ በኵራት ፥ የእጅ ፡ ማንሣታችንን ፡ ቍርባን ፥ የዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ፍሬ ፥ ወይኑንና ፡ ዘይቱንም ፡ ወደ ፡ ካህናቱ ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ ጓዳዎች ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፥ ሌዋውያኑም ፡ ከከተማዎቻችን ፡ ዕርሻ ፡ ኹሉ ፡ ዓሥራት ፡ ይቀበላሉና ፡ የመሬታችንን ፡ ዓሥራት ፡ ወደ ፡ ሌዋውያን ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፡ ማልን ።

38 ፤ ሌዋውያኑም ፡ ዓሥራቱን ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ ካህኑ ፡ ከሌዋውያን ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ ሌዋውያኑም ፡ የዓሥራቱን ፡ ዓሥራት ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጓዳዎች ፡ ወደዕቃ ፡ ቤት ፡ ያምጡት ።

39 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የሌዊ ፡ ልጆችም ፡ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ የዘይቱንም ፡ የማንሣት ፡ ቍርባንን ፡ የመቅደሱ ፡ ዕቃዎችና ፡ የሚያገለግሉት ፡ ካህናት ፡ በረኛዎቹና ፡ መዘምራኑ ፡ ወዳሉባቸው ፡ ጓዳዎች ፡ ያግቡት ፤ እንዲሁም ፡ የአምላካችንን ፡ ቤት ፡ ከቶ ፡ አንተውም ።

____________________ መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ የሕዝቡም ፡ አለቃዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ፤ ከቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ከዐሥሩ ፡ ክፍል ፡ አንዱ ፡ በቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፥ ዘጠኙም ፡ በሌላዎች ፡ ከተማዎች ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።

2 ፤ ሕዝቡም ፡ በፈቃዳቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለመቀመጥ ፡ የወደዱትን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ባረኩ ።

3 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡት ፡ የአገሩ ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እስራኤል ፡ ግን ፡ ካህናቱም ፡ ሌዋውያኑም ፡ ናታኒምም ፡ የሰሎሞንም ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየርስታቸውና ፡ በየከተማቸው ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ተቀመጡ ።

4 ፤ ከይሁዳና ፡ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ። ከይሁዳ ፡ ልጆች ፤ ከፋሬስ ፡ ልጆች ፡ የመላልኤል ፡ ልጅ ፡ የሰፋጥያስ ፡ ልጅ ፡ የአማርያ ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የዖዝያ ፡ ልጅ ፡ ዐታያ[245] ፤

5 ፤ የሴሎናዊውም ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የዮያሪብ ፡ ልጅ ፡ የዓዳያ ፡ ልጅ ፡ የዖዛያ ፡ ልጅ ፡ የኮልሖዜ ፡ ልጅ ፡ የባሮክ ፡ ልጅ ፡ መዕሴያ ።

6 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡት ፡ የፋሬስ ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስምንት ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ።

7 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የየሻያ ፡ ልጅ ፡ የኢቲኤል ፡ ልጅ ፡ የመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ የቆላያ ፡ ልጅ ፡ የፈዳያ ፡ ልጅ ፡ የዮእድ ፡ ልጅ ፡ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡ ሰሉ ።

8 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ጌቤና ፡ ሳላይ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶም ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

9 ፤ አለቃቸውም ፡ የዝክሪ ፡ ልጅ ፡ ኢዮኤል ፡ ነበረ ፤ የሐስኑአም ፡ ልጅ ፡ ይሁዳ ፡ በከተማው ፡ ላይ ፡ ኹለተኛ ፡ ነበረ ።

10 ፤ ከካህናቱ ፤ የዮያሪብ ፡ ልጅ ፡ ዮዳዔ ፥ ያኪን ፥

11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የአኪጦብ ፡ ልጅ ፡ የመራዮት ፡ ልጅ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡

245ዕብ. ፥ ዐታያህ ።



www.ethiopianorthodox.org

የኪልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፥

12 ፤ የቤቱንም ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፤ የመልክያ ፡ ልጅ ፡ የፋስኮር ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የአማሲ ፡ ልጅ ፡ የፈላልያ ፡ ልጅ ፡ የይሮሐም ፡ ልጅ ፡ ዓዳያ ፥

13 ፤ ወንድሞቹም ፡ የአባቶቹ ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ኹለት ፤ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ የምሺሌሞት ፡ ልጅ ፡ የአሕዛይ ፡ ልጅ ፡ የዔዝርኤል ፡ ልጅ ፡ ዐማስያ ፥

14 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፤ አለቃቸውም ፡ የሐግዶሊም ፡ ልጅ ፡ ዘብድኤል ፡ ነበረ ።

15 ፤ ከሌዋውያንም ፤ የቡኒ ፡ ልጅ ፡ የዐሳብያ ፡ ልጅ ፡ የዐዝሪቃም ፡ ልጅ ፡ የዐሱብ ፡ ልጅ ፡ ሻማያ ፤

16 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በሜዳ ፡ በነበረው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ የሌዋውያን ፡ አለቃዎች ፡ ሳባታይና ፡ ዮዛባት ፤

17 ፤ በጸሎትም ፡ ጊዜ ፡ ምስጋናን ፡ የሚቀነቅኑ ፡ አለቃው ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ የዘብዲ ፡ ልጅ ፡ የሚካ ፡ ልጅ ፡ መታንያ ፥ በወንድሞቹም ፡ መካከል ፡ ኹለተኛ ፡ የነበረ ፡ በቅበቃር ፥ የኤዶታምም ፡ ልጅ ፡ የጋላል ፡ ልጅ ፡ የሳሙስ ፡ ልጅ ፡ ዐብድያ ።

18 ፤ በቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ የነበሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ አራት ፡ ነበሩ ።

19 ፤ በሮቹንም ፡ የሚጠብቁ ፡ በረኛዎቹ ፥ ዐቁብና ፡ ጤልሞን ፡ ወንድሞቻቸውም ፥ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

20 ፤ ከእስራኤልም ፡ የቀሩት ፡ ከካህናትና ፡ ከሌዋውያንም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየርስታቸው ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ።

21 ፤ ናታኒምም ፡ በዖፌል ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ሲሐና ፡ ጊሽጳ ፡ በናታኒም ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።

22 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከነበሩ ፡ መዘምራን ፡ ከአሣፍ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የሚካ ፡ ልጅ ፡ የመታንያ ፡ ልጅ ፡ የሐሸብያ ፡ ልጅ ፡ የባኒ ፡ ልጅ ፡ ዖዚ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሌዋውያን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

23 ፤ ስለ ፡ እነርሱም ፡ የንጉሥ ፡ ትእዛዝ ፡ ነበረ ፤ የመዘምራኑም ፡ ሥርዐት ፡ ለየዕለቱ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ።

24 ፤ ከይሁዳም ፡ ልጅ ፡ ከዛራ ፡ ወገን ፡ የሜሴዜቤል ፡ ልጅ ፡ ፈታያ ፥ ስለሕዝቡ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

25 ፤ ስለ ፡ መንደሮቹና ፡ ስለ ፡ ርሻቻቸው ፤ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዐያሌዎች ፡ በቂርያትአርባቅና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዲቦንና ፡ በመንደሮቿም ፥ በይቀብጽኤልና ፡ በመንደሮቿም ፥

26 ፤ 27 ፤ በኢያሱ ፥ በሞላዳ ፥ በቤትጳሌጥ ፥ በሐጸርሹዓል ፥

28 ፤ በቤርሳቤሕና ፡ በመንደሮቿ ፥ በጺቅላግ ፥

29 ፤ በምኮናና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዐይንሪሞን ፥

30 ፤ በጾርዓ ፥ በየርሙት ፥ በዛኖዋ ፡ በዓዶላም ፡ በመንደሮቻቸውም ፥ በለኪሶና ፡ በዕርሻዎቿ ፥ በዓዜቃና ፡ በመንደሮቿ ፡ ተቀመጡ ። እንዲሁ ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከሄኖም ፡ ሸለቆ ፡ ድረስ ፡ ሰፈሩ ።

31 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ከጌባ ፡ ዠምሮ ፡ በማክማስ ፥ በጋያ ፥

32 ፤ በቤቴልና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዐናቶት ፥ በኖብ ፥

33 ፤ 34 ፤ በሐናንያ ፥ በሐጾር ፥ በራማ ፥ በጊቴም ፥ በሐዲድ ፥

35 ፤ በስቦይም ፥ በንበላት ፥ በሎድ ፥ በኦኖ ፥ በጌሐራሺም ፡ ተቀመጡ ።

36 ፤ በይሁዳም ፡ ከነበሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ዐያሌ ፡ ክፍሎች ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ ኾኑ ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ምዕራፍ ፡ 12 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ ከሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ከዘሩባቤልና ፡ ከኢያሱ ፡ ጋራ ፡ የወጡት ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤

2 ፤ ሰራያ ፥ ኤርምያስ ፥ ዕዝራ ፥ አማርያ ፥

3 ፤ መሉክ ፥ ሐጡስ ፥ ሴኬንያ ፥ ሬሁም ፥ ሜሪሞት ፥

4 ፤ 5 ፤ አዶ ፥ ጌንቶን ፥ አብያ ፥ ሚያሚን ፡

6 ፤ መዓድያ ፥ ቢልጋ ፥ ሸማያ ፥ ዮያሪብ ፥ ዮዳዬ ፥

7 ፤ ሰሉ[246] ፥ ዐሞቅ[247] ፥ ኬልቅያስ[248] ፥ ዮዳዬ ፤ እነዚህ ፡ በኢያሱ ፡ ዘመን ፡ የካህናቱና ፡ የወንድሞቻቸው ፡ አለቃዎች ፡
ነበሩ ።

8 ፤ ሌዋውያኑም ፤ ኢያሱ ፥ ቢንዊ ፥ ቀድምኤል ፥ ሰራብያ ፥ ይሁዳ ፥ ከወንድሞቹም ፡ ጋራ ፡ በመዘምራን ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡
መታንያ ።

9 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ በቅቡቅያና ፡ ዑኒ ፡ በየሰሞናቸው ፡ በአንጻራቸው ፡ ነበሩ ።

10 ፤ ኢያሱም ፡ ዮአቂም[249]ን ፡ ወለደ ፥ ዮአቂምም ፡ ኤልያሴብን ፡ ወለደ ፥ ኤልያሴብም ፡ ዮአዳን ፡ ወለደ ፥

11 ፤ ዮአዳም ፡ ዮናታንን ፡ ወለደ ፥ ዮናታንም ፡ ያዱአን ፡ ወለደ ።

12 ፤ በዮአቂምም ፡ ዘመን ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ካህናቱ ፡ ነበሩ ፤ ከሰራያ ፡ ምራያ ፥

13 ፤ ከኤርምያስ ፡ ሐናንያ ፥ ከዕዝራ ፡ ሜሱላም ፥

14 ፤ ከአማርያ ፡ ይሆሐናን ፥ ከመሉኪ ፡ ዮናታን ፥

15 ፤ ከሰበንያ ፡ ዮሴፍ ፥ ከካሪም ፡ ዓድና ፥ ከመራዮት ፡ ሔልቃይ ፥

16 ፤ ከአዶ ፡ ዘካርያስ ፥ ከጌንቶን ፡ ሜሱላም ፥

17 ፤ ከአብያ ፡ ዚክሪ ፥ ከሚያሚን[250] ፡ ሞዐድያ ፥

18 ፤ ፈልጣይ ፥ ከቢልጋ ፡ ሳሙስ ፥ ከሸማያ ፡ ዮናታን ፥

19 ፤ ከዮያሪብ ፡ መትናይ ፥ ከዮዳዬ ፡ ያዚ ፥

20 ፤ ከሳላይ ፡ ቃላይ ፥ ከዐሞቅ ፡ ዔቤር ፥

21 ፤ ከኬልቅያስ ፡ ሐሸብያ ፥ ከዮዳዬ ፡ ናትናኤል ።

22 ፤ ከሌዋውያኑም ፡ በኤልያሴብና ፡ በዮአዳ ፥ በዮሐናንና ፡ በያዱአ ፡ ዘመን ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡
ተጻፉ ፤ ካህናቱም ፡ በፋርሳዊው ፡ በዳርዮስ ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ ተጻፉ ።

23 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ እስከኤልያሴብ ፡ ልጅ ፡ እስከዮሐናን ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በታሪክ ፡
መጽሐፍ ፡ ተጻፉ ።

24 ፤ የሌዋውያኑም ፡ አለቃዎች ፤ ሐሸብያ ፥ ሰራብያ ፥ የቀድምኤልም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ ዳዊት ፡ ትእዛዝ ፡ በየሰሞናቸው ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያከብሩና ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ።

25 ፤ መታንያ ፥ በቅቡቅያ ፥ ዐብድዩ[251] ፥ ሜሱላም ፥ ጤልሞን ፥ ዐቁብ ፡ በበሮች ፡ አጠገብ ፡ የሚገኙትን ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡
ለመጠበቅ ፡ በረኛዎች ፡ ነበሩ ።

26 ፤ እነዚህ ፡ በኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ ልጅ ፡ በዮአቂም ፡ በአለቃውም ፡ በነሐምያ ፡ በጸሓፊውም ፡ በካህኑ ፡

---

246ዕብ. ፥ ሰሉ ፡ (የተሰላ ፥ የተለካ) ።
247ዕብ. ፥ ዐሞቅ ፡ (ዕመቅ • ጥልቀት ፣ ጒድጓድ) ።
248ዕብ. ፥ ኂልቂያህ ፡ (የጌታ ፡ ክፍል) ።
249ዕብ. ፥ ዮያቂም ፡ (ያቀውም ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ያቆማል) ።
250 ዕብ. ፥ ሚንያሚን ፡ (እምየማን • ከቀኝ) ።
251 ዕብ. ፥ ያባድያህ ፡ (ዐብደ ፡ እግዚእ ፥ የጌታ ፡ አገልጋይ) ።



www.ethiopianorthodox.org

በዕዝራ ፡ ዘመን ፡ ነበሩ ።

27 ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ በቀደሱ ፡ ጊዜ ፡ ቅዳሴውን ፡ በደስታና ፡ በምስጋና ፡ በመዝሙርም ፡ በጸናጽልም ፡ በበገናም ፡ በመሰንቆም ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጧቸው ፡ ዘንድ ፡ ሌዋውያኑን ፡ በየስፍራቸው ፡ ኹሉ ፡ ፈለጉ ።

28 ፤ 29 ፤ መዘምራኑም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ መንደሮች ፡ ሠርተው ፡ ነበርና ፥ የመዘምራኑ ፡ ልጆች ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያና ፡ ከነጦፋውያን ፡ መንደሮች ፥ ከቤትገልገላም ፥ ከጌባና ፡ ከዓዝሞት ፡ ዕርሻዎች ፡ ተሰበሰቡ ።

30 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ ራሳቸውን ፡ አነጹ ፤ ሕዝቡንም ፡ በሮቹንም ፡ ቅጥሩንም ፡ አነጹ ።

31 ፤ የይሁዳንም ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ ላይ ፡ አወጣኋቸው ፤ አመስጋኞቹንም ፡ በኹለት ፡ ታላላቅ ፡ ተርታ ፡ አቆምኋቸው ፤ አንዱም ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ወደጉድፍ ፡ መጣያው ፡ በር ፡ ኼደ ።

32 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ሆሻያ ፥ የይሁዳም ፡ አለቃዎች ፡ እኩሌታ ፥

33 ፤ ዐዛርያስ ፥ ዕዝራ ፥

34 ፤ ሜሱላም ፥ ይሁዳ ፥ ብንያም ፥ ሸማያ ፥ ኤርምያስ ፥

35 ፤ መለከትም ፡ ይዘው ፡ ከካህናቱ ፡ ልጆች ፡ ዐያሌዎች ፥ የአሣፍም ፡ ልጅ ፡ የዘኩር ፡ ልጅ ፡ የሚካያ ፡ ልጅ ፡ የመታንያ ፡ ልጅ ፡ የሸማያ ፡ ልጅ ፡ የዮናታን ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስ ፥

36 ፤ ወንድሞቹም ፡ ሸማያ ፥ ዔዝርኤል ፥ ሚላላይ ፥ ጊላላይ ፥ መዓይ ፥ ናትናኤል ፥ ይሁዳ ፥ ዐናኒ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡ የዳዊትን ፡ የዜማውን ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ኼዱ ፤ ጸሓፊውም ፡ ዕዝራ ፡ በፊታቸው ፡ ነበረ ።

37 ፤ በምንጭም ፡ በር ፡ አቅንተው ፡ ኼዱ ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ደረጃ ፥ በቅጥሩም ፡ መውጫ ፥ ከዳዊትም ፡ ቤት ፡ በላይ ፡ እስከውሃው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ኼዱ ።

38 ፤ ኹለተኛውም ፡ የአመስጋኞቹ ፡ ተርታ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ኼደ ፤ እኔና ፡ የሕዝቡም ፡ እኩሌታ ፡ በስተኋላቸው ፡ ነበርን ፤ በቅጥሩም ፡ ላይ ፥ በእቶኑ ፡ ግንብ ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ ሰፊው ፡ ቅጥር ፡ ድረስ ፥ ከኤፍሬምም ፡ በር ፡ በላይ ፥

39 ፤ በአሮጌው ፡ በርና ፡ በዓሣ ፡ በር ፡ በሐናንኤልም ፡ ግንብ ፥ በሃሜአ ፡ ግንብ ፡ እስከበጎች ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ኼዱ ፤ በዘበኛዎችም ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ቆሙ ።

40 ፤ እንዲሁ ፡ ኹለቱ ፡ የአመስጋኞች ፡ ተርታዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ቆሙ ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ እኔና ፡ የአለቃዎች ፡ እኩሌታ ፥

41 ፤ ካህናቱም ፡ ኤልያቄም ፥ መዕሴያ ፥ ሚንያሚን ፥ ሚካያ ፥ ኤልዮዔናይ ፥

42 ፤ ዘካርያስ ፥ ሐናንያ ፡ መለከት ፡
ይዘው ፥ መዕሴያ ፥ ሸማያ ፥ አልዓዛር ፥ ዖዚ ፥ ይሆሐናን ፥ መልክያ ፥ ዔላም ፥ ኤጽር ፡ ቆምን ። መዘምራኑም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ዘመሩ ፥ አለቃቸውም ፡ ይዝረሕያ ፡ ነበረ ።

43 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አሠኝቷቸዋልና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፥ ደስም ፡ አላቸው ፤ ሴቶቹና ፡ ልጆቹም ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ የኢየሩሳሌምም ፡ ደስታ ፡ ከሩቅ ፡ ተሰማ ።

44 ፤ ይሁዳም ፡ በአገልጋዮቹ ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፥ የካህናቱንና ፡ የሌዋውያኑን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ከከተማዎች ፡ ዕርሻዎች ፡ ያከማቹ ፡ ዘንድ ፡ ለእጅ ፡ ማንሣት ፡ ቊርባንና ፡ ለበኵራት ፡ ለዓሥራትም ፡ በየዕቃ ፡ ቤቶቹ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሰዎች ፡ ተሾሙ ።

45 ፤ እነርሱም ፡ መዘምራኑና ፡ በረኛዎቹም ፡ የአምላካቸውን ፡ ሥርዐት ፡ የመንጻታቸውንም ፡ ሥርዐት ፡ እንደ ፡ ዳዊትና ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠበቁ ።

46 ፤ አስቀድሞም ፡ በዳዊትና ፡ በአሣፍ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዜማ ፡ ለማመስገንና ፡ ለማክበር ፡ የመዘምራን ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

47 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በዘሩባቤልና ፡ በነሐምያ ፡ ዘመን ፡ ለመዘምራኑና ፡ ለበረኛዎቹ ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸውን ፡ በየዕለቱ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይሰጡ ፡ ነበር ፤ የተቀደሰውንም ፡ ነገር ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጡ ፥ ሌዋውያኑም ፡ ከተቀደሰው ፡ ነገር ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ሰጡ ።

## መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሙሴን ፡ መጽሐፍ ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ አነበቡ ፤ አሞናውያንና ፡ ሞዐባውያንም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዳይገቡ ፡ የሚል ፡ በዚያ ፡ ተገኘ ።

2 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በእንጀራና ፡ በውሃ ፡ ስላልተቀበሏቸውና ፡ ይረግማቸው ፡ ዘንድ ፡ በለዓምን ፡ ስለ ፡ ገዙባቸው ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካችን ፡ ርግማኑን ፡ ወደ ፡ በረከት ፡ መለሰው ።

3 ፤ ሕጉንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ድብልቁን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከእስራኤል ፡ ለዩ ።

4 ፤ ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ ጓዳዎች ፡ ላይ ፡ ተሾሞ ፡ የነበረው ፡ ካህኑ ፡ ኤልያሴብ ፡ ከጦብያ ፡ ጋራ ፡ ተወዳጅቶ ፥

5 ፤ ለሌዋውያን ፥ ለመዘምራን ፥ ለበረኛዎቹ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባንና ፡ ዕጣኑን ፥ ዕቃዎቹንም ፥ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ የዘይቱንም ፡ ዓሥራት ፥ ለካህናቱም ፡ የኾነውን ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ አስቀድሞ ፡ ያስቀመጡበትን ፡ ታላቁን ፡ ጓዳ ፡ አዘጋጅቶለት ፡ ነበር ።

6 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በአርጤክስስ ፡ በሠላሳ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ኼጄ ፡ ነበርና ፥ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አልነበርኹም ። ከጥቂት ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ የንጉሡን ፡ ፈቃድ ፡ ለመንኹ ፤

7 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጣኹ ፤ ኤልያሴብም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ለጦብያ ፡ ጓዳውን ፡ በማዘጋጀት ፡ ያደረገውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አስተዋልኹ ።

8 ፤ እጅግም ፡ አስከፋኝ ፤ የጦብያንም ፡ የቤቱን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ከጓዳ ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ጣልኹ ።

9 ፤ ጓዳዎቹንም ፡ እንዲያነጹ ፡ አዘዝኹ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ዕቃዎች ፡ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ መልሼ ፡ በዚያ ፡ አገባኹ ።

10 ፤ ለሌዋውያንም ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ እንዳልተሰጠ ፥ የሚያገለግሉትም ፡ ሌዋውያንና ፡ መዘምራን ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ዕርሻው ፡ እንደ ፡ ኼዱ ፡ ተመለከትኹ ።

11 ፤ እኔም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተተወ ፧ ብዬ ፡ ከአለቃዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተከራከርኹ ። ሰበሰብኳቸውም ፥ በየስፍራቸውም ፡ አቆምኳቸው ።

12 ፤ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ የዘይቱንም ፡ ዓሥራት ፡ ወደዕቃ ፡ ቤቶች ፡ አመጡ ።

13 ፤ በዕቃ ፡ ቤቶችም ፡ ላይ ፡ ካህኑን ፡ ሰሌምያን ፥ ጸሐፊውንም ፡ ሳዶቅን ፥ ከሌዋውያኑም ፡ ፈዳያን ፡ ሾምኹ ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የመታንያ ፡ ልጅ ፡ የዘኩር ፡ ልጅ ፡ ሐናን ፡ ነበረ ፤ እነርሱም ፡ የታመኑ ፡ ኾነው ፡ ተገኙ ፥ ሥራቸውም ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ማከፋፈል ፡ ነበረ ።

14 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ዐስበኝ ፤ ለአምላኬም ፡ ቤት ፡ ያደረግኹትን ፡ ወረታዬን ፡ አታጥፋ ።

15 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ በይሁዳ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የወይን ፡ መጥመቂያን ፡ የሚረግጡትን ፥ ነዶም ፡ የሚከመሩትን ፥ የወይኑን ፡ ጠጅና ፡ የወይኑን ፡ ዘለላ ፡ በለሱንም ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ዐይነት ፡ ሸክም ፡ በአህያዎች ፡ ላይ ፡ የሚጭኑትን ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚያስገቡትን ፡ አየኹ ፤ ገበያ ፡ ባደረጉበትም ፡ ቀን ፡ አስመሰከርኹባቸው ።

16 ፤ ደግሞም ፡ በርሷ ፡ የተቀመጡ ፡ የጢሮስ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እነርሱም ፡ ዓሣዎችን ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ዐይነት ፡ ሸቀጥ ፡ አምጥተው ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ይሸጡ ፡ ነበር ።

17 ፤ ከይሁዳም ፡ ታላላቆች ፡ ጋራ ፡ ተከራከርኹና ፦ ይህ ፡ የምታደርጉት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ የሰንበትንስ ፡ ቀን ፡ ታረክሳላችኹን ፧

18 ፤ አባቶቻችኹ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ አልነበረምን ፧ አምላካችንስ ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በእኛና ፡ በዚህ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ከተማ ፡ ላይ ፡ አምጥቶ ፡ አልነበረምን ፧ እናንተም ፡ ሰንበትን ፡ በማርከሳችኹ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መዓትን ፡
ትጨምራላችኹ ፡ አልኋቸው ።

19 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሰንበት ፡ በፊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ ድንግዝግዝታ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ በሮቿ ፡
እንዲዘጉ ፥ ሰንበትም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ እንዳይከፈቱ ፡ አዘዝኹ ። በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ሸክም ፡ እንዳይገባ ፡
ከብላቴናዎቼ ፡ በዐያሌዎቹ ፡ በሮቿን ፡ አስጠበቅኹ ።

20 ፤ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውጭ ፡ ዐድረው ፥ ገበያ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

21 ፤ እኔም ፡ አስመሰከርኹባቸውና ፦ በቅጥሩ ፡ ውጭ ፡ ለምን ፡ ታድራላችኹ ፧ እንደ ፡ ገና ፡ ብታደርጉት ፡ እጆቼን ፡
አነሣባችኋለኹ ፡ አልኋቸው ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አልመጡም ።

22 ፤ ሌዋውያኑንም ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲያነጹ ፥ መጥተውም ፡ በሮቹን ፡ እንዲጠብቁ ፥ የሰንበትንም ፡ ቀን ፡ እንዲቀድሱ ፡
ነገርኋቸው ። አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ዐስበኝ ፥ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ ብዛት ፡ ራራልኝ ።

23 ፤ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ የአዛጦንና ፡ የዐሞንን ፡ የሞዐብንም ፡ ሴቶች ፡ ያገቡትን ፡ አይሁድ ፡ አየኹ ።

24 ፤ ከልጆቻቸውም ፡ እኩሌቶቹ ፡ በአዛጦን ፡ ቋንቋ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፥ በአይሁድም ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ አያውቁም ፡
ነበር ።

25 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ተከራከርኹ ፥ ረገምኋቸውም ፤ ከነርሱም ፡ ዐያሌዎቹን ፡ መታኹ ፥ ጠጕራቸውንም ፡
ነጨኹ ፥ እንዲህም ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አማልኋቸው ። ሴቶች ፡ ልጆቻችኹን ፡ ለወንዶች ፡ ልጆቻቸው ፡
አትስጡ ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ለእናንተና ፡ ለልጆቻችኹ ፡ አትውሰዱ ።

26 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ኀጢአት ፡ አድርጎ ፡ የለምን ፧ በብዙ ፡ አሕዛብም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡
ርሱ ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፥ በአምላኩም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነበረ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡
አንግሦት ፡ ነበር ፤ ርሱንም ፡ እንኳ ፡ እንግዳዎች ፡ ሴቶች ፡ አሳቱት ።

27 ፤ በእውኑ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡ እንሠራ ፥ እንግዳዎችንም ፡ ሴቶች ፡ በማግባት ፡ አምላካችን ፡ እንበድል ፡
ዘንድ ፡ እናንተን ፡ እንስማ ፧

28 ፤ ከዋነኛውም ፡ ካህን ፡ ከኤልያሴብ ፡ ልጅ ፡ ከዮአዳ ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ ለሖሮናዊው ፡ ለሰንባላጥ ፡ ዐማች ፡
ነበረ ፤ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ አባረርኹት ።

29 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ክህነትን ፡ የክህነትንና ፡ የሌዋውያንንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስላፈረሱ ፡ ዐስባቸው ።

30 ፤ ከእንግዳ ፡ ነገርም ፡ ኹሉ ፡ አነጻኋቸው ፤ ለካህናቱና ፡ ለሌዋውያኑም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየሰሞናቸው ፥

31 ፤ በየጊዜያቸውም ፡ ለዕንጨት ፡ ቍርባን ፡ ለበኵራቱም ፡ ሥርዐት ፡ አደረግኹ ። አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በመልካም ፡ ዐስበኝ ፨



www.ethiopianorthodox.org